Oct 10, 2014

# ጉልበቴን ይያዝ

ለጸሎት የሚያነሳሳኝና በልቤ ላይ በሚደረሳ ሜለኩ ታትሞ የሚገኝ ቃል ኢሳይያስ 27፡5-6 ነው፡፡ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ስላጠናሁትም፣ለነፍሴ ሜልሕቅ ሆኗል ማለት እችላለሁ፡፡እጅግ በጣም ግሩም ቃል ነውና እርሱን ላስቀድም፡፡እንዲህ ይነበባል፡-

*ወይም ጉልበቴን ይያዝ፣ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ፤ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርግ።በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፣ እስራኤልም ያብባል ይጨፍጨፍማል፤ በፍሬያቸውም የዓለማ ፊት ይሞላሉ።* (ኢሳይያስ 27፡5-6)

*"ጉልበቴን ይያዝ"* የሚለው ቃል በሌሎች መጽሐፍ ቅዱሶች ላይ *"ማሸሸጊያው ያድርገኝ"* የሚል ትርጉምን ይዟል፡፡ *"ጉልበቴን ይያዝ ከእኔም ጋር ሰላም ያድርግ"* የሚለው ሃሳብ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረትና ቁርኝት ከሰላማችን ጋር የተያያዘ መሆኑን በግልጽ ያሳየናል፡፡አዎ! የጌታን ጉልበት በጸሎት በያዝን ቁጥር ሰላማችን እየበዛ፣እየተረጋጋን እና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እየተለወጥን ማማጣታችን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ይህንን ለ 16 ዓመት በተግባር ዳስሼ አይቼዋለሁ፡፡ኢየሱስ *"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፣ ወደ እኔ ኑ፣እኔም አሳርፋችኋለሁ"*(ማቴዎስ 11፡28) ያለንም ለዚህ ነው፤ሌላ የሚያሳርፉ የሚመስሉ ነገሮች ከሸንገላ የዘለለ ዘለቄታዊ ዕረፍት እንደሌላቸው ሲያበስረን!

ከመቼውም ዘመን ይልቅ የእግዚአብሔርን ጉልበት በጸሎት ማያዝ ያለበት ዘመን ቢኖር የአሁኑ ዘመን ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ለምን ቢባል የሰው ልጅ የክፋት ማጠን በኃይል እየጨመረ ስለመጣ ነው፡፡ሰይጣን ከእያንዳንዱ ክፋት በስተጀርባ በታላቅ ቁጣ ምድሪቷን እያማሳት ስላለ ነው፡፡ይህ ሁኔታ ደግሞ በውጭ ባሉት በማያምኑ ሰዎች ሕይወት ብቻ ሳይሆን ጌታን እናውቃለን በሚሉት ላይ በገሃድና በብዛት ስለሚታይ ያለወን የክፋት ማጠን በኃይል ያተልቀዋል፡፡በአሁኑ ሰዓት በክርስትያን ወገኖች ማሃል፡-

ፍቅርና መዋደድ እጅግ ቀዝቅዟል

ወሸት ነግሷል

ግብዘኝነት ሰፍኗል

ራስ ወዳድነት አግጦ ወጥቷል

አለመተማመን በዝቷል ….ሌላም ሌላም(ዝርዝሩ ረጅም ነው)

ከዚህም የተነሣ የሰዎች ልብ ስብራት ከማጠን በላይ እየበዛ ነው፡፡እናም ያለንበትን ዘመን አስፈሪነት ቋንቋ የሚገልጸው አይመስለኝም፡፡ለዚህ ነው በተመሳሳይ ሁኔታ ወስጥ የነበሩትን የናሆም ዘመን ሰዎች የጌታ መንፈስ *"የሚቀጠቅጥ ባንተ ላይ ወጥቷል፣ምሽግህን ጠብቅ፣መንገድህን ሰልል፣ወገብህን አጽና፣ኃይልህን እጅግ አበርታ"* (ናሆም 2፡1) ብሎ የመከራቸው፡፡እጅግ ግሩም ምክር! *"ኃይላችንን እጅግ ማበርታት"* የምንችልበት ዋነኛው መንገድ ደግሞ የጌታን ጉልበት በጸሎት ስንይዝ ነው፡፡ደምጹን ስንሰማ ነው፡፡የወስጡ ሰውነታችን ዕለት ተዕለት ሲታደስ (2 ቆሮንቶስ 4፡16) ነው፡፡ከቃሉም ጋር ስንጣበቅ ነው፡፡

ከላይ እንደጠቀስሁት *"ቀናቹ ክፉዎች ናቸውና"* (ኤፌሶን 5፡16) የጌታን ጉልበት በጸሎት ማያዝን ግድ ይለናል፡፡ታዲያ ጉልበቱን ይዘን መጮጭ ስንል፣ካልባረከኸኝ አልለቅህም ስንለወና ጥራት ያለው ጊዜን በፊቱ ስናሳልፍ፣ያኔ፡-

መንፈሳችን ይጠነክራል

አረማመዳችን ይጸናል

እምነታችን ያድጋል

በምናየው ነገር ማሽበራችን ይወገዳል

ሚጋጋት የሕይወታችን ማለጫ ይሆናል

የራዕይ ሰዎች እንሆናለን

የበረከት ሰዎች እንሆናለን

በዚህ ቃል ላይ የተጠቀሰው የሜጨሻው አስደናቂም ፍሬ "በፍሬአቸውም የምድርን ፊት ይሞላሉ" የሚል ነው፡፡እጅግ በጣም አስደናቂ ወጤት ነው፡፡እጅግ የሚገርም ተፅዕኖ ነው፡፡ እስቲ ይህ በተግባር ሆኖ ለሰከንድ በአይነ ህሊናችሁ እዩት፡፡ይህ ሲሆን የሜይነካ የሜሕበረሰብ መዋቅር የለም፡፡ይህ ሲሆን ብዙ ሰዎች ጉልበታቸውን ለጌታ ያንበረክካሉ፡፡ይህ ሲሆን ብዙ መንፈሳዊና ማሕበራዊ ችግሮች ይወገዳሉ፡፡ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር በማከላችንም ሆነ በውጭ ባሉት ዘንድ በሚገባ ይከበራል፡፡

ባጭሩ ቃሉ አራት መንፈሳዊ እመርታዎችን በግልጽ ያሳየናል(ማስሰቢያ፡-ጉብዝ አራቱም እመርታዎች የተያያዙ ናቸውና መዝለል አይቻልም)

የእግዚአብሔርን ጉልበት በጸሎት ማያዝ

ከሱ ጋር ለሜሄድ ማስማማት

ጠፍማ መንፈሳዊ ዕድገት

መንፈሳዊ ፍሬዎች

በቃሉ ወስጥ ያለው መንፈሳዊ ሂደት እጅግ ድንቅ ነው፡፡እንደተጠቀሰው እመርታዎቹ ተያያዥነት ያላቸው ስለሆኑ፣የእርሱን ጉልበት በማያዝ ጀምረን ወደ ፍሬ እንደምንመጣ ሊስተዋል ይገባል፡፡በፍጹም ሌላ አቋራጭና አሜራጭ መንገድ እንደሌለ ሊታወቅ ይገባል፡፡እዚህ ጋ ነው ዋጋ የምንከፍለው፡፡እዚህ ጋ ነው ዲሲፐሊን የምንጠየቀው፡፡እዚህ ጋ ነው ትልቁ ትግል ያለው፡፡እዚህ ጋ ነው ተስማሞቶ ለሜሄድ መወሰኛው፡፡እዚህ ጋም ነው ብዙ ረብ የሌላቸውን ነገሮች ለመጣል የምንገደደው፡፡እዚህ ጋ ነው እንደ ሃና በመንፈስ የምንቃትተው፡፡እዚህ ጋ ነው እንደ ያዕቆብ እስኪነጋ ነገር የምንፋለመው፡፡ስለዚህ እዚህ ጋ የሚከፈለውን ዋጋ ሳናቅማማ ብንከፍል፣ከኪሳራና ከወድቀት እንጠበቃለን፡፡እናም እሱ በፍሬና በበረከት ተገልጦ ያስደንቀናልና ጉልበቱን በጸሎት እንያዝ!!

በቀለ በላቸው(ዶ/ር)

beke_abay@yahoo.com

240-330-5004